ለ) አዲስ የዕጽዋት ዝርያ አዳቅሎ ያወጣና በተገኘው አዲስ ዝርያ ላይ ማሻሻያ ያደረገ ሰውን ቀጥሮ ወይም ሥራውን ተከናትሮ ያሰራ፣ ወይም

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሱትን ሰዎች መብት ተክቶ የያዘ፣ ሰው ነው፤

፬/ "ለማጓጓዝ የተዘጋጀ ጭነት" ማለት በአንድ የዕጽዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ብቻ ከአንዱ አገር ወደ ሌላ አገር የሚጓጓዝ ዕጽዋት ወይም የዕጽዋት ምርት መጠን ነው፤

፭/ "መያዣ" ማለት ከረጢት፣ ጠርሙስ፣ ኬሻ፣ ሳጥን፣ በርሜል፣ ሻንጣ ወይም ቦርሳ፣ ቆርቆሮ፣ መጠቅለያ ያለው መያዣ ወይም ሌላ ዘር ለማስቀመጥ የሚያገለግል መያዣ ነው፤

፮/ "ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ" ማለት ለተለያዩ የሰብል አይነቶች የወጣውን ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ መስፈርት እጩ ዝርያው ማሟላት አለማሟላቱ የሚረጋገጥበት የሙከራ አይነት ነው፤

፯/ "የማሳ ቁጥጥር" ማለት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በወጣው የዘር ማሳ መስፈርት መሰረት ማሳው ደረጃውን ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ሕጋዊ የማሳ ቁጥጥር ነው፤

፰/ "የመስክ መስፈርት" ማለት ዘርን በመስክ አምርቶ ለማጽደቅ አስፈላጊ የሆኑ መርሀ ግብሮች አካል ሆኖ ከሌላው ተመሳሳይ ሰብል ዓይነት/ኦፍታይፕ ያለው የአጎራባች ማሳ ርቀት፣ የሰብል ፈረቃ፣ በማሳው ውስጥ የሚገኝ የተለየ ዝርያና ኦፍታይፕ፣ አረምና በሽታ የሚያካትት መስፈርት ነው፤

፱/ "ኦፍታይፕ" ማለት አንድ ዕጽዋት ከሚታወቅበት የእድገት እና ውጫዊ መገለጫዎች ማለትም በቅጠሉ ወይም አበባው፣ በቀለሙ ወይም በቅርጹ ወይም ቁመቱ የመሳሰሉት ተቀባይነት ካገኘው ከዝርያው ባህርያት ለወጥ ብሎ የታየ ከሆነ

b) employed or commissioned a person who has bred or discovered and developed a new plant variety; or

c) a successor in title of the person specified in paragraphs (a) and (b) of this sub-article;

4/ "consignment" means a quantity of plants and plant products covered and being moved from one country to another by a single phytosanitary certificate;

5/ "container" means a bag, bottle, sack, box, barrel, case, tin, receptacle wrapper or other materials in which the seed is placed or packed;

6/ "distinctness, uniformity and stability testing" means an evaluation of whether a candidate variety meets the distinctness, uniformity and stability criteria set for the particular species of crop;

7/ "field inspection" means an official inspection of a seed field to check compliance with field standards set by Ethiopia Standard Agency;

8/ "field standards" includes requirements for isolation distance from other variety/off-types, crop rotation , disease, shedding pollen and weeds when growing crop as part of the seed certification programme;

9/ "off-type" means a plant which doesn't display the recognized characters of growth, morphological formation either in leaf or flower, a shape or color or height is in any way obviously different from accepted

፲፰/ "የዘር ሰርተፍኬሽን" ማለት ለሽያጭ የሚቀርበው ዘር ሕጋዊ የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት የጥራት ማረጋጋጫ ሥርዓት ነው፤

፲፱/ "መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት" ማለት ወጥነት ያለው እና በአካል ሊለይ የሚችል መጠኑ የታወቀ ዘር ነው።

## ክፍል ሁለት

## ዝርያን ስለመልቀቅና ስለመመዝገብ

### ፫. ዝርያዎችን ለመልቀቅ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

፩/ እጩ ዝርያዎች ከመለቀቃቸው በፊት ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ እና ዝርያውን ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መስፈርቶቻቸው መገምገም አለባቸው።

፪/ የዝርያው ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሲገመገም የሚከተሉትን ባሕሪያት ማሟላት አለበት፦

ሀ) በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ባህሪያት ከሌሎች ከተለቀቁ ዝርያዎች በግልጽ የሚለይ፤

ለ) በባህሪው ወጥነት ያለው፤ እና

ሐ) በተደጋጋሚ ሲባዛ የማይቀየር ባህሪ ያለው።

፫/ ዝርያውን ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሲገመገም የሚከተሉትን ባህሪያት ማሳየት አለበት፦

ሀ) ከተለቀቁት ዝርያዎቸ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ እንደ ምርት መጠን፣ ብሽታን የመቋቋም ብቃት፣ ሰብል የሚደርስበት ወቅት እና በመሳሰሉት ባህሪያት መብለጡን፤

ለ) በተጠቃሚዎች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ መፈለጉን።

### ፬. ዝርያ ለማስለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ ማንኛውም ሰው ዝርያ ለማስለቀቅ ዝርያው ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ያለው ስለመሆኑ እና ብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ እንዲሰራለት ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

18/ "seed certification" means a quality assurance system whereby seed intended for marketing is subject to official control and inspection;

19/ "seed lot" means a specified quantity of seed, which is homogeneous and physically identifiable.

## PART TWO

## VARIETY RELEASE AND REGISTRATION

### 3. Criteria for Release

1/ The distinctness, uniformity and stability and value for cultivation and use characteristics of the candidate varieties shall be evaluated before their release.

2/ The distinctness, uniformity and stability evaluation of the variety shall fulfill the following characteristics:

a) clearly distinguishable from all the other existing varieties in one or more characteristics;

b) uniform in its characteristics; and

c) stable in repeated multiplication cycles.

3/ The value for cultivation and use characteristics evaluation of the variety shall show they following characteristics:

a) superior to existing varieties in one or more characteristics such as amount of yield, resistance to disease, maturity and other similar characters;

b) highly desirable by users.

### 4. Application for Variety Release

1/ Any person who applies to release a variety shall submit his application to the Ministry for distinctness, uniformity and stability and national performance trial test.

፫/ ለሁለት የምርት ወቅቶች ቢያንስ ሶስት ተመሳሳይነት ባላቸው ሥነ-ምህዳር ቦታዎች ላይ ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ እና የብሔራዊ ዝርያ ሙከራ ያካሂዳል፤

፬/ ዝርያው ከኢትዮጵያ ውጪ ከዚህ በፊት የተለቀቀ ሆኖ አገር ውስጥ ለማስገባት የተፈለገ ከሆነ ተስማሚ በሆነ ሥነምህዳር ዝርያው ለእርሻ ሥራ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራዎችን ቢያንስ ለአንድ የሰብል ወቅት ያካሂዳል፤

፭/ ለብሔራዊ ዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ተልዕኮአቸውን እንዲወጡ የሎጂስቲክ ድጋፍ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

፮/ የብሔራዊ ዝርያ ብቃት ሙከራ ገምጋሚ የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ ይተነትናል፣ የማጠቃለያ ሪፖርትም ያዘጋጃል፣ እንዲሁም ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሪፖርት ይቀበላል፣ የብሔራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ስብሰባን ያዘጋጃል፤ የስብሰባውንም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤

፯/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሰረት የጸደቁ ዝርያዎችን በብሔራዊ የዝርያ መዝገብ ላይ ያሰፍራል፤

፰/ ከመንግስት የምርምር ተቋማትና ማንኛውም የሕዝብን ጄነቲክ ሀብት ተጠቅሞ ዝርያን ያጎለበተ የግሉ ዘርፍ ለእያንዳንዱ ለተለቀቀ አዲስ ዝርያ ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ አስፈላጊውን የዘር መጠን ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

፱/ በሕጋዊ መንገድ የተለቀቁትን ዝርያዎች የአራቢ ዘር ምርትንና ዝርያው ባህሪውን ጠብቆ እንዲቆይ መደረጉን ይከታተላል፤

፲/ የብሔራዊ ዝርያ መዝገብ ዝርዝርን በየጊዜው ክለሳ ያደርጋል፤

3/ perform both distinctness, uniformity and stability and national performance trial for a minimum of two seasons in at least three sites having similar agro-ecology;

4/ perform both value for cultivation and use and distinctness, uniformity and stability test for at least one season in related agro-ecological zone, for importation of a variety that has already been released outside of the Ethiopia;

5/ arrange and provide logistical support to National Performance Trial Evaluation Technical Committees;

6/ receive, analyze and compile the National Performance Trial Evaluation Technical Committee reports as well as receive results of distinctness, uniformity and stability and organize National Variety Release Committee meetings and minute its deliberations;

7/ enter approved varieties in the National Variety Register in accordance with Article 10 of this Regulation;

8/ ensure that the required quantity of seed of each newly-released variety from public research and any private sector which develop variety form public genetic resources is submitted to the Institute of Biodiversity Conservation for long time storage;

9/ follow up the quality of breeder seed production and varietal maintenance services for officially released crop varieties;

10/ ensure that the National Variety Register is reviewed on a regular basis;

፬/ ከጭነቱ ጋር የጤንነት ሰርተፍኬት ማቅረብ፤

፭/ ስለ ዘሩ ዓይነትና የዝርያ ስም እንዲሁም የዘሩ ምንጭ አገር ስም የያዘ የግዥና የርክክብ ሰነድ ማቅረብ፤ እና

፮/ ጭነቱ አስፈላጊ የሆኑ የማሸጊያና የመለያ ምልክት አለጣጠፍ መስፈርት ማሟላቱን ማረጋገጥ፤

አለበት።

፴፭. ከውጭ የሚገባ ዘር ማሟላት ያለበት መስፈርት

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት የሚቻለው፦

ሀ) የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከሚኒስቴሩ ከጋር በመተባበር ያወጣውን የኢትዮጵያ ዘር ደረጃዎች፤ እና

ለ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰነውን ማንኛ ውንም መስፈርት፣

አሟልቶ ሲገኝ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዘር ለግለሰብ ግቢ ማስጌጫ ለማዋል የሚገባ ዘር ከሆነ የመስፈርቱን አፈጻጸም ለመተው ይችላል።

፴፮. ዘርን ወደ አገር ውስጥ የማስገቢያ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ ዘርን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፦

ሀ) የአስገቢው ስምና አድራሻ፣ ዘሩ የሚመጣበት አገር እና የጭነቱ መጨረሻ መድረሻ ቦታ የሚያሳይ መግለጫ፤

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፬ እና በአንቀጽ ፴፭ (፩) የተመለከቱ አግባብ ያላቸው ሰነዶች፤

ሐ) የዘሩ ዓይነት፣ ዝርያና የዘር መጠን የሚያሳይ መግለጫ፤

4/ accompany phytosanitary certificate with the consignment;

5/ produce invoice and receipt document containing the species and variety name and the country of origin of seed; and

6/ ensure that the consignment meets all packaging and labeling requirements.

35. Requirements for Seed to be Imported

1/ Without prejudice to Article 17 of the Proclamation, seed may be imported when it meets:

a) the Ethiopian seed standards set by the Ethiopian Standard Agency in cooperation with the Ministry;

b) any other requirement set by the directive of the Ministry.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the Ministry may waive the requirements for small amounts of seed imported for private compound aesthetic purpose.

36. Application to Obtain Seed Import Permit

1/ An application to obtain seed import permit from the Ministry shall be submitted by accompanying with the following information:

a) statement showing the name and address of importer, country of origin of seed and consignment's final destination;

b) relevant documents specified under Article 34 and Article 35 (1) of this Regulation;

c) statement showing species, variety and quantity of seed;

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፩ መሠረት የዘር አዘጋጅ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው፦

ሀ) ተስማሚ የሆነ የዘር ማከማቻ መጋዘን፤

ለ) ዘር የማዘጋጀት ሥራ ለመሥራት አስፈላጊ የሆነ ማሽነሪ ወይም የሰዉ ኃይል፤ እና

ሐ) ስለዘር አዘገጃጀት መሠረታዊ እውቀት እና ልምድ ያላቸው ሠራተኞች፤

ያሉት መሆን ይኖርበታል።

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፩ መሠረት የዘር አስመጭ፣ ላኪ ወይም አከፋፋይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው፦

ሀ) ተስማሚ የሆነ የራሱ ወይም የተከራየው የዘር ማከማቻ መጋዘን፤ እና

ለ) ስለዘር አያያዝ መሠረታዊ ዕዉቀት እና ልምድ ያለዉ ባለሙያ፤

ሊኖረው ይገባል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ ዝርዝር መስፈርት እና የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፵፫. የማመልከቻ አቀራረብ**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፵፩ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፦

፩/ የአመልካቹ ሙሉ ስምና አድራሻ፤

፪/ እንደአግባቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፪ መሠረት የተመለከቱ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው ዝርዝር መረጃ፤

፫/ ሌሎች በሚኒስቴሩ መመሪያ የሚገለጹ መረጃዎች።

**፵፬. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት**

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ ክፍል የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እና የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም እንደ አግባቡ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ባለሥልጣን አማካይነት የሚሰጥ ይሆናል።

2/ Any person submitting application pursuant to Article 41 of this Regulation to obtain seed processors certificate of competence shall have:

a) suitable warehouse facilities for seed storage;

b) requisite machinery and manpower to perform the processing activities; and

c) a professional with basic knowledge and experience in seed processing.

3/ Any person submitting application pursuant to Article 41 of this Regulation to obtain seed importer, exporter and distributor certificate of competence shall have:

a) his own or rented suitable warehouse facilities for seed storage; and

b) a professional with basic knowledge and experience in seed handling.

4/ Without prejudice to sub-articles (1), (2) and (3) of this Article, the Ministry may issue directive on the detail criteria and implementation procedures.

**43. Submission of Applications**

Any application submitted pursuant to Article 41 of this Regulation to obtain a certificate of competences shall be accompanied with the following information:

1/ the applicants full name and address;

2/ detail information on the compliance of requirements specified under Article 42 of this Regulation, as the case may be;

3/ other information specified in the directive of the Ministry.

**44. Issuance of Certificate of Competence**

1/ A certificate of competence may be issued by the Ministry or by the regional authority when the requirements provided for in this Part are complied with and upon payment of service fee.

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሶስተኛ ወገን በማንኛውም መልኩ ሊተላለፍ ወይም ሊሰጥ አይችልም።

፫/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት እና የሚታደስበት ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፭. የዘር ኢንስፔክሽን

፩/ ሚኒስቴሩ፦

ሀ) ለዘር ኢንስፔክተሮች ምደባ የሚያገለግል ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት እና ልምድ በመመሪያ ይወስናል፣ አቅማቸውን ለማጎልበት ሥልጠና ይሰጣል፤

ለ) የዘር ኢንስፔክተሮች ሥራቸዉን በአግባቡ ማከናወን እንዲችሉ ደረጃዉን የጠበቀ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ ያዘጋጃል።

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ (፪) የተመለከቱ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የዘር ኢንስፔክተር፦

ሀ) በመስክ የዘር ጥራት ፍተሻ በማከናወን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የተቀመጠዉ የኢትዮጵያ ደረጃ ስለመሟላቱ ቁጥጥር ያደርጋል፤

ለ) የዘሩን ጥራት ለማረጋገጥ በድቃይ ሰብል ላይ ቢያንስ ሦስት ጊዜና በሌሎች ሰብሎች ቢያንስ ሁለት ጊዜ የመስክ ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) የመስክ ቁጥጥር ለተደረገበት ለእያንዳንዱ ማሳ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

መ) የመስክ ቁጥጥርን ያለፈ ዘር ወደ ዘር ማዘጋጃ ቦታ ከመጓጓዙ በፊት በመያዣ ዕቃዉ ላይ የማይለቅ የቀለም ምልክት በማድረግ ያረጋግጣል፤

ሠ) ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዓላማ የተመዘገበ ዘር አምራች ማሳን፣ የዘር አዘገጃጀትን እና የዘር ማከማቻ መጋዘንን የጥራት ቁጥጥር ፍተሻ ያደርጋል።

2/ A certificate of competence may not be transferred or assigned in any form to a third party.

3/ The validity period of certificate of competency and its renewal shall be prescribed in directive to be issued by the Ministry.

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 45. Seed Inspection

1/ The Ministry shall:

a) issue directive to determine the minimum qualification and experience needed for the assignment of seed inspectors; and provide training to develop their capacity;

b) prepare standard operational guidelines and directive for the seed inspectors to carry out their functions.

2/ Without prejudice to the responsibilities provided for under Article 23 (2) of the Proclamation a seed inspector shall have responsibilities to:

a) conduct field inspection on seed and inspect whether it meets the Ethiopian standard prescribed by Ethiopian Standards Agency;

b) conduct at least three field inspections on hybrid crop and at least two field inspections on other crops;

c) prepare a report for each field on which inspection is conducted;

d) ensure seed passed field inspection by putting mark with indelible ink on the container before it is transported to the processing place; and

e) conduct quality control inspection of the registered seed producer's field, seed processing and storage warehouse for the purpose of certification.

**፵፮. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፵፯. ደንቡ የሚፀናበት ቀን**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**46. Inapplicable Regulations**

No regulation shall, in so far as it is in consistent with this Regulation, have effect in respect of matters provided for in this Regulation.

**47. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 18th day of February, 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**